# <u>መዘክር</u>

## <u>ካሣ ምርጫ</u>

ምነው አጤ ጉድ አረጉን
ለጣልያን ተስማምተው የሸጡን፣
ምነው አጤ ተዋረዱ
በደርቡሽ አንገትዎን ታረዱ፣
የእርስዎ ታሪክ ያለቀለት
ሞክሼ ካሣን የከዱ ዕለት።

ለግልዎ ሥልጣን ሲፈልጉ
ለጦር መሣሪያና ኃይል ሲጓጉ፣
ጀነራል ናፒየርን መንገድ መርተው
ቃለ መሐላዎን ሁሉ አፈራርሰው፣
ንጉሡን እጃቸውን ሊያስይዟቸው
እስከ መጨረሻው ከድተዋቸው።

ንጉሡ ቴዎድሮስ ግን ቆራጥ ጀግና
እጄን እንዳልሰጥ አሉና፣
ከጋሻጃግሬዎቻቸው ሳይለዩ ሲሰዉላት
“ትንሣኤ ሰንደቅ ዓላማ” ለአገራቸው
ሲያስነሱላት፣
ዓለም ያደነቀው ይኸ ነው ጀግንነት
በታላቅ ክብር ሲወሳለት።

ለጊዜው በተገኘው መሣሪያ ተደራጅተው
እርስዎም ሥልጣንዎን አመቻችተው
ንጉሥ ሲሆኑ አጤ ተብለው፣
ተዲያ መንግሥዎስ ጥሩ ነበር
ከበፊቱ የወረሱት ዳር ድንበር
አኩሪ ታሪክ የኢትዮጵያ በር።

እየዋለ እያደረ በቂልነት
ጣልያኖች በተደጋጋሚ ሲያታልልዎት፣
መሣሪያ ገንዘብ እንደተለመደው
እየሰጥዎት
የሆነው ይሁን ምን ጨነቅዎት፣
አገርዎን እየቆራረሱ ሲያስወስዱት
ዳር ድንበርዎን ሲያስደፍሩት።

ለአገራቸው ክብር ተቆርቋሪ
የጦር አመራር አበጣሪ፣
ለአንድነት ዳር ድንበሯ ሊሞቱላት
ጀግኖች ሳያጡ ሊሰዉላት፣
እነአሉላን አስቀምጠው
ደርቡሽ ከወደሰሜን መጣ ብለው
ታሪክዎም በከንቱ ያበቃው።

ጀግኖችዎን ካላመኑ
የአገርዎን ክብር ካልመጠኑ፣
አንድነቷ እንዲጠበቅ ሳያደርጉ
መልካም አመራር ሳይፈልጉ፣
ይኸው እስከዛሬ በዚያው መዘዝ
ከችግሩ ሳንላቀቅ ስንጓዝ፣
እንዲህ ተከፋፍለን አለንልዎ
በሉ እግዜር ነፍስዎን ይማርልዎ።

ዓለማየሁ አስፋው/ ቶሮንቶ